# <u>አስተውሎ ላየው ይህም አንድ እድል ነው</u> !



ከ-አብዶ ኑር የሱፍ
(ኖርዌይ)

ድሮ ድሮ አምባገነኖች ለምን አይሞቱም ? የሚል ጥያቄ በውስጤ ይመላለስ ነበር ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የአምባገነኖችን ሞት መስማት የተለመደ እየሆነ መጥቷል ። በሃገራችን ለብዙ ሳምንታት እንደ ሚስጢር ተይዞ የነበረው የቀድሞው የወያኔ ጠቅላይ ሚኒስትር ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን የኢትዮጵያ ቴልቪዥን በማለዳ አወጀ።ይህ መርዶ ለአንድአንዶች የጠበቁት ባይሆንም እውነታውን ግን እንዲቀበሉት ተገደዋል።

ቀደም ሲል በመንግስት ቃል አቀባዮች እና ለቤተ መንግስት ቅርበት ባላቸው ግለሰቦች አማካኝነት ሰውየው አልታመሙም በሙሉ ጤንነት ላይ ናቸው ይህ የኢሳት ወሬ ነው ቢሉም በአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ላይ የሰውየው መታመም ባልፈለጉት ሁኔታ ከተገለፀባቸው ወዲህ የወያኔ የፕሮፖጋንዳ ጋዜጣዎች እንደ ሪፖርተር ፣ አዲስ አድማስ ፣ፎርቹን እና የድርጅቱ አፍቃሪ ድህረ ገጾች በየፊናቸው እውነታውን እያወቁት ሃገር ቤት ገብተዋል ፣ቤተመንግስት እያገገሙ ነው ፣ አሜሪካ እየተዝናኑ ነው የሚሉ ግራ የሚያጋቡ እና የተሳሳቱ መረጃዎችን ለህዝቡ ሲያስተላልፉ ቢቆዩም የመለስ ዜናዊ መሞት ተረጋግጦ ነገሩ የኢሳት ወሬ ከመሆን አልፎ ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥንም የመሰንበቻ ወሬ ሆነ ። ምንም እንኳን አቶ በረከት ስምኦን ልባቸው እያወቀ በ ኤስ.ቢ.ኤስ ሬዲዮ ቀርበው ለአዲሰ አመት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የእንኳን አደረሳችሁ ንግግር እንደሚያደርጉ ቢዋሹም የ2005 አዲስ አመት ሳይገባ የቀብር ስነ ሰራአታቸው እንድሚፈፀም በአንደበታቸው በድጋሚ አወጁ ።

ሌላው ለወያኔዎች አስደንጋጭ የሆነው ዜና ከወያኔ ጋር በመተባበር ከ20 አመት በፊት በህይወት ያሉትን ጳጳስ በማስወገድ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በጉልበት ሲመሩ የነበሩት አቡነ ጳውሎስ ለሚመሩት ቤተ እምነት አንድም ቀን ሳያስቡ እንዲሁም ስለ ታሪካዊ ገዳማችን ዋልድባ መፈራረስ ምንም ሳይተነፍሱ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በተመሳሳይ ወቅት ወደ ማይቀረው አለም መሰናበታቸው ተሰማ ። ፍቅር እስከ መቃብር ማለት ይህ አይደል ? ፈጣሪያችን ምን አይነት መልእክት ማስተላለፍ ፈልጎ ይሆን ? ልናስተውል ይገባናል ። ሁለቱም ሟቾች የኢትዮጵያ ህዝብ እና ታሪክ ጠላት ከመሆናቸው በተጨማሪ የሚያመሳስላቸው ብዙ ነገሮች አሉ ጥቂቶቹን ለማስታወስ ያህል በየፊናቸው ስልጣን ላይ የቆዩት በጉልበት ያለ ህዝብ ፍላጎት ነበር ፣ ሁለቱም ተመሳሳይ የፖለቲካ አራማጆች ነበሩ ፣ሁለቱም ተቃዋሚዎቻቸውን ሲያስገድሉ እና ሲያሳድዱ የቆዩ ነበሩ ፣ሁለቱም ግለሰቦች የትውልድ ቦታቸው አንድ መሆኑ እንዲሁም ሁለቱም እንደ በረከት ስምኦን አይነት የውሸት ቃል አቀባይ እና አጃቢዎች ነበሩዋቸው ።

የሰው ልጅ ሞት የሚያስደስት ነገር ባይሆንም የግለሰቦቹ መሞት በተለይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ባደረሱት ኢሰብአዊ ግፍ እና በደል እንዲሁም በህዝቡ ዉስጥ በዘሩት የዘረኝነት መርዝ እና ባራመዱት ፀረ- ኢትዮጵያ አቋም የግለሰቡ ሞት የወያኔ መንግስት ለፈጠረው አስከፊ ስርአት መገርሰስ በር ከፋች ሊሆን ይችላል ። በሌላ በኩል ከድርጅቱ እና ከግለሰቡ ተጠቃሚ የነበሩ ግለሰቦች አንጀታቸዉ ተቃጥሎ ባገኙት አጋጣሚ እንደአበደ ዉሻ ያገኙትን እየተናከሱ ይገኛሉ ። ለዚህም በጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ላይ በካንጋሮው የወያኔ ፍርድ ቤት ነሀሴ 17 ,2004 ዓ.ም የተወሰደው እርምጃ ተጠቃሽ ነው።

ይህ በእንዲህ እያለ የአቶ መለስ ዜናዊ ሞት ከታወጀ በኃላ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ያየኃቸው ትእይንቶች በጣም አስገርመውኛል በተለይ አትሌት ሃይሌ ገብረስላሴ ንግግር ሲያደርግ እና ሲያለቅስ ሳየው ከወያኔ ጋር እየተጓዘ ባለበት መንገድ ተፀፅቶ ይሆን ? ወይስ ምን አይነት የጠቅላይ ሚኒስትሩን ጥሩ ስራ አስታውሶ ነው ? እና ሌሎችም ጥያቄዎች በአእምሮዬ ተመላለሱ እውነታው ወደፊት የሚወጣ ይሆናል። ሌላው በሀገራችን «በሽምግልና » የታወቁትን ፕሮፌሰር ይስሀቅን በቤተ መንግስተ ሳያቸው ወይዘሮ አዜብ መስፍንን ለቅሶ ለመድረስ ሳይሆን በስልጣን ሽሚያ የትጣሉትን የወያኔ አንጃዎችን ለማስታረቅ የመጡ ነበር የመሰለኝ ።

በተጨማሪ የታዘብኩት ነገር የወያኔ ደጋፊ የሆኑት ባለሀብት ሼህ አልአሙዲን በአቡነ ጳውሎስ የቀብር ስነስርአት እንዲሁም በአቶ መለስ ዜናዊ አስክሬን አቀባበል ዝግጅት ላይ አለመገኘታቸው ሰሞኑን በኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች ላይ የገባው ፈንግል በሽታ ሰለባ ሆነው ይሆን እንዴ ? ወይስ የወያኔ ስርአት በቅርብ እንደሚገረሰስ ስላወቁ ከወያኔ መራቅ ፈለጉ ? ሚስጢሩ ወድፊት የሚፈታ ይሆናል ።

በተንኮል የድራማ ዝግጅት የሚታወቀው የወያኔ ቡድን በዚህ እለትም የሰሩት ድራማ የተሳካላቸው ይመስላል። አስክሬኑ ከቤልጂም ከመግባቱ በፊት የወያኔ ካድሬዎች ስራ በዝቶባቸው ውለው ነበር። በአዲስ አባባ እና አካባቢዋ የሚገኙ የሴቶች ማህበራት ፣ የመንግስት ሰራተኞች ፣ የወጣቶች ሊግ እና በጥቃቅን እና አነስተኛ የተደራጁ ወጣቶችን በግዳጅ እና በጉልበት የሰውየውን አስክሬን እንዲቀበሉ ጥብቅ ጥሪ ተላልፎላቸው በቦሌ አወሮፐላን ማርፊያ በመገኘት የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሞት የህዝቡ ሃዘን ለማስመሰል ተሞክሯል ። አንድአንዶቹም « ጀግና አይሞትም »፣«እኛን ለማን ትተህ» የሚሉ ስላቆችን አሰምተዋል ። ምናምን በበላበት ይጮሃል አይደል የሚባለው ? በጣም የሚገርመው በህይወት እያሉ በቦሌ ጎዳና ላይ ህዝብ እንዳያያቸው የቆመ መኪና እንኳን ሳይቀር በማስነተት የሚያስነሱት መለስ ዜናዊ ከሞቱ በኃላ አስክሬናቸው በዚህ ጎዳና ላይ በነፃነት ማለፉ ደጋፊዎቻቸው እንደ 5 አመቱ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ውጤት ይቆጥሩት ይሆን ?

መለስ ዜናዊ በመሞታቸው ሀገራችን ኢትዮጵያ ትልቅ መሪ እንዳጣች እና ወደፊትም የማይተኩ ስዩመ እግዚአብሄር እንደነበሩ አድርገው፣በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ተወዳጅ መሪ እንደነበሩ ለማስመሰል በየቀበሌው ድንኳን ተዘጋጅቶ ህዝቡ ተገዶ እንዲያለቅስ እናም ቪዲዮ ተቀርፆ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በማስተላለፍ ላይ ይገኛል ። ከዚህ በተጨማሪ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ዜጎችን በማስገደድ ጥቁር ልብስ ለብሰው ስላማዊ ስልፍ እንዲወጡ ለማድረግ በካድሬዎቹ አማካኝነት ማዋከቡን ቀጥለዋል ። ይህንንም ለህዝብ ለማስተላለፍ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ልዑካኖች ወደተመረጡ ትልልቅ ከተማዎች ተጉዘዋል ። ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሆነ ለመለስ ዜናዊ መሞት የሚያዝን እና የሚያለቅስበት አንጀቱን በአግዓዚ ሰራዊት እና በፌደራል ፖሊስ ጥይት በአደባባይ ተበጣጥሶ ከወደቀ ብዙ አመታቶችን አስቆጥሯል ። ለይስሙላ እንኳን እንዳያለቅስ በአቶ መለስ ዜናዊ የተንኮል አደረጃጀት የተዋቀረው የወያኔ ድርጅት በብለሹ አስተዳደር ፣በዘረኝነት ፣በስራ አጥነት ፣በፍትህ እጦት፣ በአሸባሪነት የውሸት ክስ ፣በኑሮ ውድነት ፣ በስደት ፣በእስራት ,,,ወዘተ ለ21 አመታት ስላሰለቀሰው አሁን የሚያነባው እንባ የለውም ።

ከሁሉም በላይ ያስደነቀኝ የወይዘሮ አዜብ መስፍን የሀዘን እንጉርጉሮ ነው ። ወይዘሮ አዜብ መስፍን እና አንድአንድ ግለሰቦች በሃዘን በጣም የተጎዱ ይመስላሉ ።በተለይ ወይዘሮዋ ፕሮግራሙ በቀጥታ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በሚተላለፍበት ወቅት በጣም አንጀት በሚበላ ስሜት« እኔ የማያስፈልግ ቅጣት ተቀጣሁ ፣ወይኔ ተቀጣሁ ፣ወይኔ ተቀጣሁ ፣ወይኔ ተቀጣሁ ፣ቤታችን ቀዘቀዘ ፣አልጋው ባዶ ነው ,,,,ወዘተ » እያሉ ሃዘናቸውን ሲገልጡ ለሰማ ቤተሰቡን ለሚወድ፣ማንነታቸውን ለማያውቅ እና ሆደ ቡቡ ለሆነ ሰው አንጀት የሚበላ እንጉርጉሮ ነበር ።

እኔ ግን ይህንን አንጀት የሚበላ እንጉርጉሮ በምሰማበት ጊዜ ያስታውስኩት የ1997 ዓ.ም ምርጫ መጭበርበርን ተከትሎ በዛሬው ሟች መለስ ዜናዊ ቀጥተኛ አዛዥነት በአደባባይ እና በጠራራ ፀሃይ በአልሞ ተኳሾች ጥይት ጭንቅላታቸውን እና ደረታቸውን ተመተው የተገደሉትን የ14 አመቱን ታዳጊ ነበዩን ፣ ወጣትዋን ሽብሬ ደሳለኝን እና ሌሎችንም ከ200 በላይ የሆኑ የሟች ቤተሰቦችን መሪራ ሀዘን ነው ። የወይዘሮ አዜብ መስፍን ባለቤት ምን ያህል የኢትዮጵያን ህዝቦች አንጀት እንዳሳረሩ ፣ ስንቱን ወላጅ ያለ ጧሪ እና ቀባሪ እንዳስቀሩ ፣ የስንቱን አልጋ ባዶ እንዳስቀሩ ፣የስንቱን ቤት እንዳቀዘቀዙት ቤት ይቁጠረው። የቤተሰብም ሀዘን ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ባለቤታቸው በሞት ተቀድመው ሊያዩት ባይችሉም ወይዘሮዋ እና ወዳጆቻቸው ግን የሀዘንን ክብደት አይተውታል ብዬ አምናለሁ ።

በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሰራችሁት ግፍ በመብዛቱ ጨካኝ አድርጋችሁን የሞተውን ነብስ ይማር የማንልበት ደረጃ ብታደርሱንም የቤተሰብ ሃዘን ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ሰላያችሁት ተደስቻለሁ ማለት ባህላችን ባይሆንም እናንተም በማን አለብኝነት ለመራራ ሀዘን የዳረጋችኃቸውን ቤተሰቦች እና ግለሰቦች የምታስቡበት ትክክለኛ ጊዜ መሆኑን እወቁት ፡፡

በመጨረሻም ጠቅላይ ሚኒስቲሩ በሰሩት ወንጀል በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት መጠየቅ ሲገባቸው ሳይጠየቁ ፣ እንደ አምባገነን መሪነታቸው እንደነ ጋዳፊ አስክሬናቸው ሳይጎተት ፣ ደማቸው ሜዳ ላይ ሳይፈስ ፣ በካድሬዎቻቸው አማካኝነት አልቃሽ ተዘጋጅቶላቸው ፣በጉልበት ከንፈር ተመጠላቸው ፣ ጨርቅ ነው ይሉትን ስንደቅ አላማ ለብሰው እና እናት ሃገሬ ብለው ጠርተዋት በማያውቋት ሃገር ላይ ሊቀበሩ ነው፡፡ አስትውሎ ላየው ሰው ይህም አንድ እድል ነው ፡፡ ከዚህ ጥፋት የማትማሩት የመለስ ዜናዊ ፖለቲካ ርዝራዦች ራሳችሁን ለሌላ ጥፋት ከማዘጋጀት ይልቅ በአስቸኳይ ህዝቡን የስልጣን ባለቤት ማድረግ ካልቻላችሁ እና በሃገራችን እውነተኛ ዲሞክራሲ እንዲሰፍን ሁኔታውን ካላመቻቻችሁ ነገ እናንተ ይህንን እድል እንደማታገኙት እና የእነ ጋዳፊ እጣ ፋንታ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚደርስባችሁ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

***ኢትዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር !***

**<u>ለ አስተያየቶት</u> - abnuye2001@gmail.com**